washington healthplanfinder
click. compare. covered.

# የጤና ሽፋን መሰረታዊ ነገሮች

ሽፋን ስለማግኘት ማወቅ የሚያስፈልገዎ ሁሉ ነገር



# ይዘቶች


| | |
|---|---|
| 4 | Washington Healthplanfinder™ |
| 5 | ቁልፍ ቃላቶች |
| 6-7 | የጤና እቅድ መሰረታዊ ነገሮች |
| 8 | ጥቅማ-ጥቅም |
| 9 | የፋይናንስ ድጋፍ |
| 10 | Washington Apple Health (Medicaid) |
| 11 | የጤና እቅድን መምረጥ |
| 12-14 | Cascade Care |
| 15-16 | መቼ ላመልክት |
| 17 | የማመልከቻ ዝርዝር |
| 18-23 | እንዴት ማመልከት ይቻላል |
| 23 | ይከተሉን! |

# Washington Healthplanfinder™

## Washington Healthplanfinder ምንድነው?

Washington Healthplanfinder ማለት በዋሽንግተን ውስጥ በኦንላይ የጤና እቅድ የሚገዛበት ቦታ ነው። በዋሽንግተን ውስጥ ያሉ ሰዎች ለእነሱ የሚስማማ የጤና እቅድን በእኛ በኩል ማግኘት ይችላሉ።

Washington Healthplanfinder በሌላ ቦታ ሊገኙ የማይችሉትን እቅዶችን እና ቁጠባዎችን ያቀርባል። የ Cascade Care እቅዶች ከሌሎች ብዙ እቅዶች የበጠለ አገልግሎቶችን እና ቁጠባዎችን ይሰጣል። እንደ የታክስ ክሬዲት ያሉ የቁጠባ ፕሮግራሞች የእርስዎን የፕርሚየምስ (አረቦን) ወጪን ሊቀንሱ ይችላሉ። እነዚህን ጥቅማ ጥቅሞች የትም ቦታ ሊያገኟቸው አይችሉም።

## Washington Healthplanfinderን እንዴት ነው መጠቀም የሚችለው?

ከ Washington Healthplanfinder ጋር ለጤና እቅድ ማመልከት ቀላል ነው። በ wahealthplanfinder.org ላይ፣ በWAPlanfinder መተግበሪያ ወይም በስልክ መመዝገብና መግዛት ይችላሉ።

ድር ጣቢያችንን ይጎብኙ
**wahealthplanfinder.org**

## ጥያቄዎች? ለደንበኛ ድጋፍ ይደውሉ።

የደንበኛ ድጋፍ ማዕከላችን ከ200 በላይ ቋንቋዎች ድጋፍ ይሰጣል።

ይደውሉልን
ስልክ ቁጥር፦ **1-855-923-4633** | TTY፦ **1-855-627-9604**

# ቁልፍ ቃላቶች

እነዚህ ውሎች የእርስዎን የጤና እቅድ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው።

### የፕሪምየም ክፍያ

ፕሪምየም ማለት ለጤና ዕቅድዎ በየወሩ የሚከፍሉት መጠን ነው። ምንም የጤና ኢንሹራንስ እክብካቤ አገልግሎቶችን የማይቀበሉ እንኳ ቢሆን የእርስዎን ፕሪምየም የመክፈል ግዴታ አለብዎት።

### ወጭን መጋራት

ወጭን-መጋራት እርስዎ የሚከፍሉትን የጤና እንክብካቤ ወጭዎችን መጠን ይመለከታል። ይህ ውል ተቀናሾችን የጋራ-መድህን እና የጋራ ክፍያ ያካትታል።

### ተቀናሽ

ተቀናሽ ማለት የጤና እቅድዎ ወጪ መጋራት ከመጀመሩ በፊት ለእንክብካቤዎ መክፈል ያለብዎት መጠን ነው። የተቀናሽ መጠን በእያንዳንዱ ዓመት መጀመርያ ላይ ይጀምራል።

### የጋራ ክፍያ

የጋራ ክፍያ ማለት ሽፋን ላገኙበት የጤና እንክብካቤ የሚከፍሉት የክፍያ መጠን ነው። የጋራ ክፍያ የሚከፍሉት አገልግሎቱን ሲያገኙ ነው።

### የጋራ -መድህን

የጋራ መድንህን የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ለሚሸፍነው የእርስዎ የሚከፍሉት ድርሻ ነው። የጋራ መድንህን የሚከፍሉት የጤና እቅድ ተቀናሽ ከከፈሉ በኋላ ነው።

### ከኪስ የሚከፈል ክፍያ

ከኪስ የሚከፈል ክፍያ ማለት እርስዎ ለጤና እንክብካቤዎ የሚከፍሉት ክፍያ ነው። ተቀናሽ፣ የጋራ መድህንና የጋራ ክፍያ ሊያካትት ይችላል።
በጤና ዕቅድዎ ሽፋን ያላገኘ ማንኛም ክፍያ ከኪስ የሚከፈል ነው።

### ኔትዎርክ

ኔትዎርክ ማለት የጤና እቅድዎ የሚሸፍነው የአቅራቢዎች ዝርዝር ነው። የኔትዎርክ ውስጥ አቅራቢ በጤና እቅድዎ ተቀባይነት ያገኘ አቅራቢ ነው። ከኔትዎርክ ውጪ ያሉት አቅራቢዎች በጤና እቅድዎ ተቀባይነት የላቸውም።

# የጤና እቅድ መሰረታዊ ነገሮች

## የጤና እቅድ ምንድነው?

እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ የጤና እንክብካቤ ቢያስፈልግ ብለው በየዓመቱ የጤና ዕቅድ ይገዛሉ። የጤና እቅድ ካለዎት የኢንሹራንስ አገልግሎት አቅራቢዎ የጤና እንክብካቤ ወጪን በከፊል ይከፍልልዎታል።

## የጤና እቅድ ለምን ያስፈልገኛል?

ጤናማ ሰዎች ሳይቀሩ የጤና እንክብካቤ ስርዓትን ይጠቀማሉ። የጤና እቅድ ካለዎት በሚፈያስፈልግዎ ጊዜ የጤና እንክብካቤ ወጪዎች ተመጣጣኝ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ጤናማም ከሆኑ በጤናማ ሆነው ለመቆየት የመከላከያ እንክብካቤን ማግኘት ይችላሉ። ካልሆነ ደግሞ በፍትነት ህክምናን ማግኘት ይችላሉ። የጤና እቅድ በሚፈልጉበት ወቅት ህክምና እንዲያገኙ ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ያቀርብልዎታል።



### ለወደፊት የጤና እቅድ

ሀኪም ጋር መሄድ የምትፈልጉት መቼ እንደሆነ በፍፁም አያውቁም። የጤና እቅድ መኖሩ ግን በሚፈልጉበት ጊዜ የህክምና እንክብካቤ ማግኘት እንዲችሉ ያረጋግጣል።

ጤናማ የሆኑ ቢሆን እንኳ፣ የጤና እቅድዎ በጤናማነት እንዲቆዩ ይረዳዎታል።



### በጤንነትዎ እነሽስት ያድርጉ

ካለጤና እቅድ የጤና እንክብካቤ ወጭዎች ውድ ሊሆኑ ይችላሉ። መደበኛ ጉብኝቶች በፍጥነት ይጨምራሉ። የድንገተኛ ጉዳት ወይም ለከባድ ህመም የሚከፈሉ የእንክብካቤ ወጭ፣ ቁጠባዎን ሊያሟጥጠው ይችላል።

ዛሬ በጤና እቅድ ላይ ትንሽ በማውጣት ወደ ፊት ብዙ መቆጠብ ይችላሉ።

## ተመጣጣኝ የእንክብካቤ ህግ ምንድነው?

ተመጣጣኝ እንክብካቤ ህግ ከወጣ በኋላ የዋሽንግተን ግዛት Washington Healthplanfinder ፈጠረ። የተመጣጣኝ የእንክብካቤ ህግ ግቡ የጤና እንክብካቤ ወጭን መቀነስ ነው። ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ብዙ ሰዎች በትንሽ ወይም ያለ ወጭ የጤና እቅድን ለማግኘት ይችላሉ። የእርስዎ ሁኔታ ለ ዋሽንግተን አፕል ሄልዝ (ሜዲኬይድ) (Washington Apple Health (Medicaid)) ወይም ለሽፋን የሚከፍሉትን መጠን መቀነስ ጥቅማ-ጥቅሞች ብቁ ያደርግዎታል።

ለነጻ ወይም ዝቅተኛ ወጭ የጤና ሽፋን በ wahealthplanfinder.org እና WAPlanfinder መተግበሪያ ማመልከት ይችላሉ።

## የጤና እቅድ ባላገኝስ?

ካለጤና እቅድ ሙሉውን የህክምና እንክብካቤ ውጭ ይከፍላሉ። የጉንፋን (ፍሉ) ክትባት 50 ዶላር ያስወጣል። የሶስት ቀናት በሆስፕታል ቆይታ አስር ሺዎችን ያጠይቃል። የካንሰር ህክምና እስከ መቶ ሺህዎች ሊጠይቅ ይችላል።

እንዲሁም ሽፋን ካላገኙ የግብር ቅጣት ሊጣልብዎ ይችላል። በዋሽንግተን ውስጥ፣ በቤተሰብዎ ውስጥ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው አንድ ያገኛሉ።

## እንክብካቤ ምን ያህል ስወጣል?

እንዳንድ የተለመዱ ህክምናዎች እና ዋጋቸው እነሆ።
እንደእነዚህ ያሉት ወጭዎችን የጤና እቅድዎ ሊጋራዎ ያችላል።

| ህክምና | ወጪ |
|---|---|
| የልብ ቀዶ ህክምና | $78,585 |
| ማሞግራም | $263 |
| የአከሪካሪ ቀዶ ህክምና | $13,255 |
| ኮሎንስኮፒ | $1,484 |
| የወሊድ ቀዶ- ህክምና | $18,098 |
| የአስቸኳይ እንክብካቤ ጉብኝት | $181 |
| አመታዊ የጤና ምርመራ (በአስራዎቹ እድሜ ለሚገኙ ለታዳጊዎች) | $117 |
| የድንገተኛ ክፍል ጉብኝት | $579 |

# ጥቅማ-ጥቅም

### የጤና እቅድን የሚሸፍነው ምንድነው?

ሁሉም የጤና እቅዶች እነዚህን አስር መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞችን ይሸፍናሉ። አንዳንድ እንደ Cascade Care እቅዶች የመሳሰሉት የበለጠ ይሸፍናሉ።

**መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥቅሞች**

- የዶክተር ጉብኝቶችና የሆስፒታል ቆይታ
- የድንገተኛ ክፍል ጉብኝቶች
- የወሊድ እንክብካቤ
- የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች እና ያለአግባብ ንጥረ ነገር ተጠቃሚ ህክምና
- በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች
- በሚጎዱበት ጊዜ የማገገሚያ አገልግሎቶች
- የላቦራቶሪ ሙከራዎች
- የመከላከል አገልግሎት
- ስር የሰደዱ የጤና ሁኔታዎች ቁጥጥር
- የሕፃናት ሕክምና

### ▶ Cascade Care

በ Cascade Care ዕቅድ ከመቼው የበለጠ ተጨማሪ አገልግሎቶች እና ቁጠባዎችን ማግኘት ይችላሉ።

### ▶ መከልከል የለም

የቆየ የጤና ሁኔታ ስላለዎት ሽፋን አይከለከሉም።

### ▶ የእንክብካቤ ጥራት

ብዙ የጤና እቅዶች እርስዎ ሽፋን በሌለዎት ጊዜ ከሚያገኙት የበለጠ ከፍተኛ ጥራት ያለው እንክብካቤ ይሰጣሉ።

### ▶ ነፃ የመከላከል እንክብካቤ

እንደ ክትትል እና ክትባት ያሉ አገልግሎቶች በሙሉ ተሸፍነዋል።

# የፋይናንስ ድጋፍ

### የታክስ ክሬዲቶች ምንድን ናቸው?

የታክስ ክሬዲቶች በእያንዳንዱ ወር ለጤና እቅድዎ የሚከፍሉትን የክፍያ መጠን ይቀንሳሉ። እነሱም በመንግስት የሚከፈሉ እና በጤና እቅድዎ ፕሪሚየም ላይ ይተገበራሉ። የታክስ ክሬዲቶች የሚገኙት በ Washington Healthplanfinder በኩል ብቻ ነው።

### የታክስ ክሬዲቶች ማግኘት የሚችል ማንነው?

የሚያገኙት የታክስ ክሬዲቶች መጠን በእርስዎ የገቢ መጠን እና በቤተሰብዎ ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። የቤተሰብዎ የገቢ መጠን ባነሰ መጠን፣ ለብዙ የታክስ ክሬድቶች መጠን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ መጠን የሚሰላው ሲመዘገቡ ነው። እነዚህ ነገሮች እውነት ከሆኑ ለታክስ ክሬዲቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦

- ለ Washington Apple Health (Medicaid) ወይም Medicare ብቁ ኤደሉም።
- በስራዎ በኩል ወይም በሌላ የመንግስት ፕሮግራም አማካይነት ኢንሹራንስ (መድን) የለዎትም።
- የዩኤስ ዜጋ ነዎት ወይም በህጋዊ መንገድ በአሜሪካ ውስጥ የሚገኙ እና በዋሽንግተን ውስጥ እየኖሩ ነው።
- ባለትዳር ከሆኑ፣ የጋብቻ ፋይል በተናጠል ለግብር ተመላሽ አያቀርቡም።

### Cascade Care Savings ምንድን ነው?

የ Cascade Care Savings ፕሮግራም የጤና እቅድ ፕሮሚየም ወጭዎን ይቀንሳል። ብቁ ከሆኑ፣ የፕርሚየምዎን የተወሰነ መጠን መንግስት ይከፍላል።

### የ Cascade Care Savings እንክብካቤ ቁጠባን ማግኘት የሚችል ማነው?

የሚከተሉት ነገሮች እውነት ከሆኑ እርስዎም ለCascade Care Savings እንክብካቤ ቁጠባ ቁጠባ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፦

- ለፌዴራሉ የድህነት ደረጃ ገቢያችሁ ከ250 በመቶ ያነሰ ነው።
- Washington Apple Health (Medicaid)፣ Apple Health Expansion ወይም Medicare ብቁ አይደሉም።
- በ Cascade Care የነሃስ ወይም የወርቅ እቅድ ተመዝግበዋል።
- ለግብር ክሬድቶች ብቁ ከሆኑ፣ ማግኘትት የሚችሉትን መጠን በሙሉ ተቀብለዋል።

# Washington Apple Health (Medicaid)

## Apple Health ምንድነው?

Apple Health ማለት በዋሽንግተን ውስጥ የMedicaid ስም ነው። እሱም ሁሉንም መሰረታዊ የጤና ጥቅማጥ-ቅሞችን ይሸፍናል። ብዙ ሰዎች ያለ ምንም ወጪ Apple Health ማግኘት ይችላሉ። አንዳንዶች ወርሃዊ ፕሪሚየም መክፈል ሊኖርባቸው ይችላል።

በማንኛው ጊዜ በWashington Healthplanfinder በኩል ለApple Health ማመልከት ይችላሉ።

## Apple Healthን ማግኘት የሚችል ማንነው?

እነዚህ ነገሮች እውነት ከሆኑ Apple Health ሊያገኙ ይችላሉ። ብቁ መሆንዎን ካላወቁ፣ አካውንት ይፍጠሩ ወይም Washington Healthplanfinder ውስጥ ይግቡ።


- ገቢዎ ከፌደራል የድህነት ወለል በ138% በታች ነው።
- የሚኖሩት በዋሽንግተን ነው።
- ከ65 ዓመት በታች ነዎት።

# የጤና እቅድን መምረጥ

### ትክክለኛውን ዕቅድ ማግኘት ቀላል ሊሆን ይችላል።

የጤና ዕቅድ በሚመረጥበት ወቅት ሊታሰብባቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ። ለብዙዎቹ እቅዶች ብቁ መሆን ይችላሉ፤ ሆኖም ለሚያስፈልግዎ ነገሮች ከሁሉ የተሻለው የትኛው እንደሆነ እርግጠኛ አይደሉም። የተለያዩ እቅዶች የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ያቀርባሉ። የCascade Care እቅዶች ለእያንዳንዱ የብረት ወለል (metal level) የተሻለ ጥቅማጥቅሞችን ለማቅረብ መደበኛ የወጭ-መጋራትን ይጠቀማል።

ከታች ያሉ ጥያቄዎች ወደ ትክክለኛው የጤና ዕቅድ ይመራዎታል።




- **በወር ምን ያህል ለመክፈል እችላለሁ?**
  ወርሃዊ ፕሪሚየም በየጤና ዕቅዶች ይለያያሉ።

- **የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤ ሀኪም መምረጥ አለብኝ?**
  አንዳንድ እቅዶች ለእርስዎ አንድ ያቀርባሉ።

- **የአሁኑ ሀኪሜ በእቅዱ ትስስር ውስጥ ነው?**
  የአሁኑ ሀኪምዎ መሸፈኑን ያረጋግጡ።

- **ኤስፔሻሊስት ለማግኘት የፅሁፍ ርፈራል ያስፈልገኛል?**
  አንዳንድ እቅዶች የፅሁፍ ርፈራል ይጠይቃሉ።

- **ሀኪሞችን ለመቀየር ምን ያህል ቀላል ነው?**
  ወደ ፊት ሀኪምን ለመቀየር ይፈልጉ ይሆናል።

- **ተቀናሽ አለ?**
  እቅድዎ ወጭዎን ከመጋራቱ በፊት ተቀናሽዎ ገንዘብዎን ማሟላት አለብዎት።

- **የዚህ እቅድ ከኪስ የሚከፈሉ ወጭዎች ምንድናቸው?**
  ከራስ ኪስ የሚከፈሉ ወጭዎች ተደጋጋሚ ጎብኝቶችን ይጨምራል።

- **ይህ እቅድ የድንገተኛ ክፍል ጉብኝቶችን እንዴት ያስተናግዳል?**
  በድንገተኛ ሰዓት ምን ማድረግ እንዳለብዎ ይወቁ።

- **በቀጣይ አመት ውስጥ የሚጠብቀው ትልቅ የህክምና ወጭ አለ?**
  ልጅ ለመውለድ ወይም ሌላ ትልቅ ወጪ እየጠበቁ ከሆነ ተጨማሪ ሽፋን ሊያስፈልግዎ ይችላል

# Cascade Care

## የCascade Care ዕቅዶች ምንድን ናቸው?

የCascade Care እቅዶች በWashington Healthplanfinder አማካይነት የሚገኙ ብቁ የጤና እቅድ አይነት ነው። አስፈላጊ የጤና ጥቅማ ጥቅሞችን ይሸፍናሉ እና ከብዙ ዕቅዶች የበለጠ አገልግሎቶችን እና ቁጠባዎችን ያቀርባሉ።

ሁለት አይነት የCascade Care እቅዶች አሉ፦ Cascade እቅዶች እና Cascade Select የተመረጡ እቅዶች (ምርጥ እቅዶች) ናቸው። የCascade Select plans ከፍተኛ ደረጃዎችን ማሟላት አለባቸው። እነሱም ከሌሎች እቅዶች የበለጠ ጥራት እና ዋጋ ያቀርባሉ።

## ለምን የCascade Care እቅድን ልምረጥ?

የ Cascade Care እቅዶች በአነስተኛ ወጭ ብዙ ሽፋንን ያቀርባል። ተቀናሹን ከማሟላትዎ በፊት ከብዙ ዕቅዶች ይልቅ የበለጠ አገልግሎቶችን ይሸፍናሉ። ይህም የመጀመሪያ እንክብካቤ፣ የአእምሮ ህመም አገልግሎቶች፣ አጠቃላይ መድሃኒቶችን እና ሌሎችንም ያጠቃልላል።

እንዲሁም ከኪስ የሚደረጉ ወጪዎችን ይቆጥባሉ። በአማካይ፣ የCascade Care ዕቅድን ከመረጡ የእርስዎ ተቀናሽ ክፍያ ከ1,000 ዶላር ያነሰ ነው።

## የCascade Care እቅዶች እንዴት ነው የሚሰሩት?

የCascade Care እቅዶች መደበኛ የወጭ መጋራት ንድፍን ጠቀማል። ይህ ማለት ጥቂት ነገሮች ነው። በመጀመሪያ፣ ከራስ ኪስ የሚደረጉ ወጪዎች በአገልግሎት አቅራቢዎች መካከል እንደነበሩ ይቆያሉ። በእያንዳንዱ የብረት ወለል ላይ ያሉ ሁሉም Cascade Care እንክብካቤ እቅዶች ተመሳሳይ ተቀናሽ፣ የጋራ ክፍያ እና የጋራ ኢንሹራንስ ይጋራሉ።

ሁለተኛ፣ የCascade Care እቅዶች ተመሳሳይ ሽፋንን ይጋራሉ። ተቀናሽ ሳይከፈል በፊት ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ይሸፍናሉ። በጣም ጥሩ ሽፋን እንዳለዎት በማወቅ በቀላሉ ማረፍ ይችላሉ።

## ተጨማሪ ምርጫዎች። ተጨማሪ እሴት።

የ Cascade እና የ Cascade Select የተመረጡ እቅዶች ተጨማሪ ምርጫዎችን እና ተጨማሪ እሴትን ይሰጥዎታል። መደበኛ የወጪ መጋራት ዲዛይናቸው ለርስዎ የሚችሉትን ምርጥ ሽፋን እንዲያገኙ ያረጋግጣል።

Cascade Care እቅዶች የሚገኙት በWashington Healthplanfinder በኩል ብቻ ነው። ብቁ እንደሆኑ ለማየት ወደ አካውንትዎ ይግቡ።



**እቅዶች በWashington Healthplanfinder ላይ ይገኛሉ።**

| | Cascade-ያልሆኑ እቅዶች | Cascade እቅዶች | Cascade Select እቅዶች |
|---|---|---|---|
| ለታክስ ክሬድትስ ብቁ የሆነ ነው | ✓ | ✓ | ✓ |
| ለCascade Care Savings ብቁ ነው | | ✓ | ✓ |
| ብቁ የሆነ የጤና እቅድ (ጥራት ያለው ደረጃዎችን ማሟላት አለበት) | ✓ | ✓ | ✓ |
| ሁሉንም አስሩን መሠረታዊ የጤና ጥቅማ ጥቅሞችን ይሸፍናል | ✓ | ✓ | ✓ |
| ወጥ የሆነ ወጪ መጋራት (እቅዶች ተመሳሳይ ተቀናሽ፥ የጋራ ክፍያና የጋራ ኢንሹራንስ) | | ✓ | ✓ |
| ተቀናሽ ሳይሟላ በፊት የመጀመሪያደረጃ እንክብካቤ፥ አስቸኳይ እንክብካቤ፥ መሠረተ-ሰፊ መድኃኒቶችና ሌሎችን ተጨማሪ ይሸፍናል። | | ✓ | ✓ |
| የሚቀርበው Washington Healthplanfinder ብቻ | | ✓ | ✓ |
| በዋሽንግተን ውስጥ በእያንዳንዱ ካውንቲ ውስጥ ይቀርባል | ✓ | ✓ | |

# መቼ ላመልክት

## ለጤና እቅድ መቼ ነው ማመልከት የምችልው?

ምዝገባ ክፍት በሚሆንበት ጊዜ ለጤና እቅድ ለማመልከት ይችላሉ። ምዝገባ ክፍት የሚሆንበት ወቅት ብቁ የጤና ዕቅዶችን እና ብቃት ያላቸውን የጥርስ እቅዶችን በWashington Healthplanfinder ላይ የሚገዛበት የዓመቱ ጊዜ ነው። እሱም በእያንዳንዱ ዓመት ኖቨምበር 1 ይጀምራል።

## ምዝገባ ክፍት ከመሆኑ በፊት ሽፋን ከፈለኩኝስ?

አንዳንድ የህይወት ለውጦች በዓመት ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለጤና እቅድ እንዲመዘገቡ ያስችሉዎታል። ይህም የተለየ ምዝገባ ይባላል። ብቁ የሆነ የህይወት ክስተት በተከሰተ ከ60 ቀናት በኋላ ለልዩ ምዝገባ ማመልከት ይችላሉ።

**ብቁ የህይወት ክስተቶች**

- ጋብቻ
- የቤት ውስጥ አጋርነት መግባት
- መውለድ
- ልጅ ማሳደግ ወይ ማደጎ እንክብካቤ
- ቀድሞ ጡረታ መውጣት
- በሞት፣ ፍቺ ወይ ሕጋዊ መለያየት ምክንያት ጥገኛ ማጣት ወይም የጥገኝት ደረጃን ማጣት
- ሌላ የጤና መድህን ማጣት
- ነፃ የCOBRA ሽፋን ማጣት
- ወደ ዋሽንግተን መዛወር
- ወደ አዲስ ካውንቲ መዛወር
- የዜግነት ሁኔት ለውጥ ወይ ሕጋዊ የአሁን ማንነት ለውጥ
- ከእስር ቤት መውጣት
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ (የልጆች ማሳደጊያ ጨምሮ) መቀበል
- የገቢ ለውጥ

## ዝቅተኛ-ገቢ ቤተሰቦች

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቡተሰቦች በየትኛውም ጊዜ የተለየ ምዝገባን መጠየቅ ይችላሉ። ብቁ ህይወት ክስተት አያስፈልግም። ይህን ጥቅም ለማግኘት ከፌደራል የድህነት ደረጃ (FPL) ከ 250% ያነሰ መሆን አለብዎት።

## የ AI/AN ግለሰቦች እና የጎሳ አባላት

የምዝገባ ህጎች በአላስካ ቤተኛ ኮርፖሬሽን (Alaska Native Corporation) ውስጥ ላሉ የጎሳ አባላት እና ባለ አክሲዮኖች ላይ ስራ ላይ አይውልም። በአመቱ በየትኛውም ጊዜ መመዝገብ ይችላሉ። እንዲሁም ለመረጡ እቅድዎን በወር አንዴ መቀየር ይችላሉ።



# የማመልከቻ ዝርዝር

## ለማመልከት ምን ያስፈልገኛል?

ለጤና እቅድ በሚመዘገቡበት ወቅት Washington Healthplanfinder ስለእርስዎ የተወሰነ መሰረተዊ መረጃን ይፈልጋል። የሚያስፈልግዎን እንዳለዎት ለማረጋገጥ ከታች ያለውን ዝርዝር ይጠቀሙ።

- ☑ **ህጋዊ ስም እና የትውልድ ቀን**
  ለሽፋን የሚያመለክቱ የእያንዳነዱ ሰው ህጋዊ ስም እና የትውልድ ቀን ያስፈልግዎታል።

- ☑ **የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሮች (SSN)**
  እያንዳንዱ የሚያመለክት ሰው ካላቸው ኤስ ኤስ ኤን እንዲዘጋጅ አድርጉ። ከሌለዎትም ማመልከት ይችላሉ።

- ☑ **ዜጋ ያልሆነ ደረጃ**
  ዜጋ ካልሆኑ ደረጃዎን ማወቅ ሊያስፈልግዎ ይችላል። ጎዳዩ ይህ ከሆነ፣ እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባላቶች አሁንም ሽፋንን ማግኘት ይችላሉ።

- ☑ **የገቢ እና የግብር ማቅረቢያ ሁኔታ**
  ለማመልከት ለእያንዳንዱ ሰው ያለዎትን ማንኛውንም የገቢ መረጃ ይሰብስቡ። ይህም የW-2 ቅጾችን እና የግብር ተመላሾችን ሊያካትት ይችላል።

- ☑ **ሌላ የኢንሹራንስ መረጃ**
  እንደ Medicare፣ Tricare ወይም ሥራ ላይ የተመሠረተ ሽፋን የመሳሰሉ ሌሎች የጤና ኢንሹራንስ አማራጮች ሊኖሩዎት ይችላሉ። ሲያመለክቱ ይህንን መረጃ ያሰባስቡ።

# እንዴት ማመልከት ይቻላል

### የሚፈልጋቸውን ሁሉንም ነገር አለኝ! ከዚህ ቀጥሎ ምንድን ነው የሚሆነው?

በ wahealthplanfinder.org ላይ ወይም በስልክ ሽፋን ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።

**ኦንላይን በ wahealthplanfinder.org ላይ ይመዝገቡ**

አካውንት ይፍጠሩ፣ የጤና ዕቅዶችን ይግዙ እና ጠቃሚ መረጃ በእኛ ድር ጣቢያ ላይ ያግኙ።

**በ 1-855-923-4633 ይደውሉልን**

የደንበኛ ድጋፍ ከሰኞ እስከ አርብ ከ7፡-30 a.m. እስከ 5፡-30 p.m. በስልክ ይገኛል።

## ጠቅ ያድርጉ። ያወዳድሩ። ተሸፍኗል።

በWashington Healthplanfinder አማካይነት ለፍላጎትዎ ተስማሚ የሆነ የጤና እቅድን ለማግኘት ቀላል ነው። wahealthplanfinder.org ወይም WAPlanfinder መተግበሪያን በመጠቀም እነዚህን ቀላል እርምጃዎች ይውሰዱ።

**1**

**ይግዙ እና ያወዳድሩ።**
እድሜዎን፣ የትምባሆ አጠቃቀም እና የገቢዎን ግምት ያቅርቡ። ሊያገኙ የሚችሉትን የጤና እቅዶች እና ፕርምየማቸውን ዝርዝር ሊያገኙ ይችላሉ።

**2**

**ያመልክቱ።**
ተጨማሪ እንደ የግብር ማስገቢያ ደረጃ እና የገቢ ምንጮችን ያሉ መረጃዎችን ያስገቡ። ይህም ለፋይናንስ ድጋፍ፣ ለWashington Apple Health (Medicaid) ወይም ለብቁ የጤና እቅድ ብቁ እንደሆኑ ለማየት ያስችልወታል።

**3**

**እቅድን ምረጡ።**
በሁኔታዎ ላይ ተመስርተው ብዙ አማራጮች ሊኖርዎ ይችላል። ለራስዎ እና ለቤተሰብዎ ፍላጎቶች ምርጡን እቅድ ምረጡ።

**4**

**ሽፋን ያግኙ።**
ሽፋንዎ የሚጀምረው የመጀመሪያ ፕሪሚየም ሲከፍሉ ነው። ከኢንሹራንስ አገልግሎት ሰጪዎ የክፍያ መጠየቂያ ደረሰኝና ካርድ ያገኛሉ።

## በማመልከቻዎ ድጋፍ ያግኙ።

በምዝገባው ሂደት ሊመሩዎት ከሚችሉ በግዛቱ ዙሪያ ካሉ ባለሙያዎች ጋር አብረን እንሰራለን። እነዚህ ባለሙያዎችም ደላሎች እና አሳሾች ይባላሉ። እነዚህ ሰዎች ስለ ጤና እቅዶች ወይም እንዴት መመዝገብ እንደሚችሉ ለጥያቄዎ መልስ ሊሰጡ ይችላሉ። እንዲሁም ለፋይናንስ ድጋፍ ብቁ ከሆኑም ሊነግርዎት ይችላሉ።

ከደላሎች እና ከአሳሾች የሚደረግ ድጋፍ ብዙ ጊዜ በነፃ ነው። በእርስዎ አካባቢ wahealthplanfinder.org ወይም በ WAPlanfinder መተግበሪያ ላይ አንድ ይፈልጉ።

## የምዝገባ ማእከላት ከአሳሾች እና ከደላሎች ጋር በከተማ

**ቤሊንግሃም**
PCF Insurance Services
2200 Rimland Dr., #305, Bellingham, WA 98226
*ስልክ ቁጥር፦* 1-360-734-1173
*ኢሜይል፦* Keith.Wallace@pcfins.com

**ኤቨርት**
Health Insurance Solutions NW, LLC
7003 Evergreen Way, Suite B, Everett, WA 98203
*ስልክ ቁጥር፦* 1-425-252-5105
*ኢሜይል፦* neil@his-nw.com

**ፌዴራል ዌይ**
የሲያትል እና ኪንግስ ካውንቲ (Seattle & King County) የማህበረሰብ ጤና
1640 S 318th Place, Federal Way, WA 98003
*ስልክ ቁጥር፦* 1-800-756-5437
*ኢሜይል፦* chap@kingcounty.gov

**ኬነዊክ**
Advisor Health Benefits Group
1446 Spaulding Ave, Suite 302, Richland, WA 99352
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-524-9611
*ኢሜይል፦* kevin@advisorhealthbenefits.com

**ሲያትል**
Financial Designs
2723 California Avenue SW, Seattle, WA  98116
*ስልክ ቁጥር፦* 1-425-392-7390
*ኢሜይል፦* cmcclure@financialdesignsinsurance.com

**ስፖካነ**
Better Health Together Enrollment Center
157 S Howard, Ste 300, Spokane, WA 99201
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-370-5605
*ኢሜይል፦* bhtnavigatorstaff@BetterHealthTogether.org
*ድር ጣቢያ፦* www.betterhealthtogether.org/navigators

---

**ታኮማ**
FND Insurance & Financial Services, LLC
5515 Steilacoom Blvd SW, Suite 122, Lakewood, WA 98499
*ስልክ ቁጥር፦* 1-253-302-5579
*ኢሜይል፦* teamfnd@fndinsurance.com

---

**ቫንኮቨር**
Applied Team Insurance
8513 NE Hazel Dell Avenue, Suite 101, Vancouver, WA 98665
*ስልክ ቁጥር፦* 1-360-726-6092
*ኢሜይል፦* marlena@appliedteamins.com

---

**ያክማ**
Yakima Neighborhood Health Services
610 Yakima East Avenue, Yakima, WA 98901
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-853-2377
*ኢሜይል፦* navigators@ynhs.org

## የምዝገባ ማዕከላት ከአሳሾች ጋር በካውንቲ

**አዳምስ፣ ፌሪ፣ ሊንከን፣ ፔንድ ኦሬይ፣ ስቲቨንስ፣ ወይም ስፖኬን ካውንቲ**
Better Health Together
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-370-5605
*ኢሜይል፦* bhtnavigatorstaff@BetterHealthTogether.org
*ድር ጣቢያ፦* www.betterhealthtogether.org/navigators

---

**ችላን፣ ዳግላስ፣ ግራንት፣ ወይም ኦካኖጋን ካውንቲ**
Confluence Health
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-433-3383
*ኢሜይል፦* sm_ch_lead_org@confluencehealth.org

---

**አሶቲን፣ ቤንቶን፣ ኮሎምቢያ፣ ፍራንክሊን፣ ጋርፊልድ፣ ዋላ ዋላ፣ ወይም ዊትማን ካውንቲ**
Greater Health Now
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-567-5317
*ኢሜይል፦* WAHBEquestions@greaterhealthnow.org

---

**ክላም ወይም ኪትሳፕ ካውንቲ**
Lutheran Community Services Northwest
*ስልክ ቁጥር፦* 1-360-452-5437(ክላላም) |1-360-377-5511(ክትሳፕ)
*ኢሜይል፦* clallamfamilycenter@lcsnw.org
kitsapfamilycenter@lcsnw.org

---

**ጄፈርሰን፣ ኪንግ፣ ወይም ስኖሆሚሽ ካውንቲ**
የሲያትል እና ኪንግስ ካውንቲ (Seattle & King County) የማህበረሰብ ጤና
*ስልክ ቁጥር፦* 1-800-756-5437
*ኢሜይል፦* chap@kingcounty.gov

---

**ኪቲታስ ወይም ያኪማ ካውንቲ**
Yakima Neighborhood Health Services
*ስልክ ቁጥር፦* 1-509-853-2377
*ኢሜይል፦* navigators@ynhs.org

**ክላርክ፣ ኮውሊትዝ፣ ግሬስ ወደብ፣ ክሊኪታት፣ ሉዊስ፣ ሜሰን፣ ፓሲፊክ፣ ፒርስ፣ ስካጊት፣ ስካማኒያ፣ ቱርስተን፣ ዋህኪያኩም፣ ወይም የዋትኮም ካውንቲ**
Sea Mar Community Health Centers
*ስልክ ቁጥር፦* 1-855-289-4503
*ኢሜይል፦* seamaripa@seamarchc.org

---

**Statewide Tribal Assister help**
American Indian Health Commission
*ኢሜይል፦* laura.kluever@aihc-wa.com




# ይከተሉን!

ጠቃሚ መረጃዎችን እና በምዝገባ ላይ አዲስ ነገርን በዚህ ማህበራዊ ድረ-አምባ ላይ እናካፍላለን።

- Washington Healthplanfinder
- waplanfinder

washington
healthplanfinder
click. compare. covered.

wahealthplanfinder.org
1-855-WAFINDER | 1-855-923-4633